# የግንቦት 7 ድምጽ

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 82 ታህሳስ 1 2002 ዓ.ም


እንደ ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ እምነት በአዲስ ነገር ጋዜጣ፣ በአዘጋጆቹና በጋዜጠኞች ላይ እየደረሰ ያለው ቅጥ ያጣ እንግልት ነገ በመላ ሕዝባችን ላይ የሚደርሰውን አመላካች ነው። ስለሆነም አፈናውን አምረን እንታገላለን።

. . . ዝርዝሩን ገጽ 2

## ወያኔ በአዲስ አበባ ውስጥ ለሚገኙ የዲፕሎማቲክ መስሪያቤቶችና የተባበሩት መንግስታት ወኪሎች የደህንነት ስጋት ይኖራል በማለት ማስጠንቀቂያ ማሰራጨቱ ታወቀ

በድህረ ምርጫ 97 በአዲስ አበባ ከተማ ብቻ ከ200 በላይ ንጹሃን ዘጎችን በአጋዚ ጦር ያስጨፈጨፈና ህዝብ አመነታ የሰጣቸውን ተመራጮች ጨምሮ ከ50ሺህ ሰዎች በላይ በየ እስር ቤቶች በዘግናኝ ሁኔታ ሲያስቃይ የነበረው ዘረኛው የመለስ አገዛዝ ሰሞኑን ለዲፕሎማቲክ ሚሽኖች እና ለተባበሩት መንግስታት መቤት ከዚህ ወር አጋማሽ ጀምሮ እስከ ሚቀጥለው ጥር ወር ባሉት ጊዜያቶች ሽብርተኞች በአድስ አበባ ከተማ ባልታወቁ ስፍራዎች የቦምብ ፍንዳታ ሽብር ለማካሄድ እየተንቀሳቀሱ ነው በማለት ማስጠንቀቂያ ማሰራጨቱን የግንቦት 7 ታማኝ የውስጥ ምንጮች አጋለጡ ።

እንደምንጮቻችን መረጃ ወያኔ ይህንን የስጋት ማስጠንቀቂያ ለመበተን የተነሳሳው ከቀን ወደቀን እያየለ በመሄድ ላይ ያለው ህዝባዊ ተቃውሞ ባልተጠበቀ ጊዜና ቦታ ሊፈነዳ እንደሚችል በመገንዘቡ ፤ አስቀድሞ እራሱ በሚያቀነባብረው የሽብር ፍንዳታ ተቃውሞውን ሊያስተባብሩ ይችላሉ ብሎ የሚጠረጥራቸውን ለመምታት በማቀዱ ነው። በሰላማዊ ትግል ወያኔን በምርጫ ሳጥን ለማሸነፍ የሚቻልበትን ምህዳር ሙሉ በሙሉ ያዳፈነው ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ፡ ህዝብ የተቀማውን መብቱንና ነጻነቱን ለማስመለስ የሚያደርገውን ሁለገብ ትግል በሽብርተኝነት በመፈርጅ፡ የስልጣን ዕድሜውን ለማራዘም የሚወስዳቸውን ፋሽስታዊ እርምጃዎች የጸረሽብርተኝነት ዘመቻ አካል በማስመሰል የአለም አቀፉን ህብረተሰብ ድጋፍ ለማግኘት እንዲቻለው ነው ተብሎአል። ቀደም ሲል ወያኔ ተመሳሳይ የፍንዳታ አደጋዎችን በተደጋጋሚ በማቀነባበር ሪዮተአለሙን የሚቃወሙትን ንጹሃን የኦሮሞ ተወላጆችን በኦነግ ሥም እየወነጀለ ሲያስር፤ ስያሰቃይና ሲገድል እንደነበረ የሚታወቅ ሲሆን ኦርሚኛ ተናጋሪ ያልሆኑትን የህብረተሰብ ክፍሎች በኦነግ አጋሪነት መፈረጅ ስላልተቻለ ሊደረግ ከታሰበው የይስሙላ ምርጫ በፊት የሚያሰጉትን ተቃዋሚዎች ለማጥቃት ታስቦ አሁን እየተወጠነ ባለው ፍንዳታ የግንቦት 7እጅ አለበት ለማለት እንደሆነ ተደርሶበታል።

## የአዲስ ነገር ጋዜጣ ቢሮ በወያኔ ደህንነቶች ተዘረፈ

ለዝርፊያ የተፈጠረው ወያኔ አዲስ ነገር በመባል ትታተም የነበረችውን ጋዜጣ ጽህፈት ቤት ሰብሮ በመግባት ኮምፒውተርና ሌሎች የኤሌክትሮኒክስ እቃዎችን መዝረፉን የጋዜጣዋን ተወካዮች ጠቅሶ ኢኤም ኤፍ የተባለው ድህረ ገጽ ዘገበ። የአዲስ ነገር ጋዜጠኞች በቅርቡ በወያኔ ሊደርስባቸው የነበረውን ጥቃት በመሸሽ ከአገር መውጣታቸው በስፋት መዘገቡ የሚታወቅ ሲሆን፣ ይህን ተከትሎ የወያኔ የደህንነት ሰዎች ወደ ጋዜጣው ጽህፈት ቤት በሀይል በመግባት የተለመደውን ዝርፊያ አካሂደዋል። የደህንነት አባላቱ የጋዜጣውን የሂሳብ ሰራተኛ አቶ ሰለሞን ደህባንና ሌሎችን ሰራተ ኞች በማስፈራራት መረጃ ለማግኘት የሞከሩ ቢሆንም ፣ የፈለጉትን መረጃ ለማግኘት ባለመቻላቸው የድርጅቱን ንብረት ዘርፈው ተመልሰዋል። የወያኔው የዘራፊ ቡድን ከአዲስ ነገር ቢሮ የዘረፈው ንብረት ዋጋ ወደ ግምሽ ሚሊዮን ብር እንደሚጠጋ ድህረገጹ አክሎ ዘግቧል።

ወያኔ ከምርጫ 97 በሁዋላ የበርካታ ጋዜጦችን ቢሮዎች በመስበር ንብረታቸውን የዘረፈ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን፣ የአብዛኞቹ ጋዜጠኞች ንብረቶች እንዳልተመለሱም ይታወቃል። የአዲስ ዜና ጋዜጣ ንብረት የነበሩ በርካታ ኮምፒዩተሮች፣ ዲጂታል ካሜራዎች፣ ስካነሮች፣ ፎ ቶ ኮፒ ማሽኖች ና የተለያዩ ማተማያዎች ተዘርፈው ለድርጅቱ እንዳልተመለሱ፣ የአስኳል፣ የሚኒሊክ፣ የሳተናው፣ የኢትዮጵና የነጻነት ንብረቶችም እንዲሁ ተዘርፈው እንደቀሩ ያገኘነው መረጃ አመልክቷል። ወያኔ ከ ድርጅቶቹ የዘረፈው ንበረት አልበቃው ብሎ ፣ ሰሞኑን ደግሞ በእነዚህ ድርጅቶች ላይ እንደገና የይገባኛል ክስ ማንቀሳቀሱን ገልጸን መዘገባችን ይታወቃል።

ነጻ ሚዲያ ለአንድ አገር የሚኖረው ጠቀሜታ ከፍተኛ መሆኑ እየታወቀ፣ የወያኔ አምባገነኖች ግን አሁንም ስለ ሚዲያ ጠቀሜታ ያላቸው እውቀት እጅግ ዝቅተኛ መሆኑ በተደጋጋሚ ሲዘገብ ቆይቶአል። ወያኔ በዘንድሮው አመት ነጻ ምርጫ አካሂዳለሁ ብሎ የሚፎክረው፣ በግንቦት 97 ምርጫ ወቅት (**ወደ ገጽ 4 ዞሯል**)

ግዜ
ግንቦት 7 ዜና

## አሜሪካ በኢትዮጵያ ያሉ ከፍተኛ የስልጣን ቦታዎች በአንድ ብሄር ሰዎች መያዛቸውን አጋለጥች፤ የአውሮፓ መንግስታትም በወያኔ አገዛዝ ላይ ያላቸውን አሳሳቢ ጥያቄ አቅርበዋል

ትናንት በተካሄደው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብአዊ መብቶች ጉባኤ ላይ የኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት አያያዝ ተገምግሞ እንደነበር የግንቦት 7 የዲፕሎማቲክ ምንጮች ገልጸዋል። ለረጅም ጊዜ በሲውዘርላንድ የወያኔው አምባሳደር የነበረውና በአሁኑ ወቅት የስዩም መስፍን ልዩ አማካሪ የሆነው ፍሰሀ ይመር የወያኔን የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ሪፖርት በማጋነን ካቀረበ በሁዋላ የተለያዩ መንግስታት ተወካዮች ጥያቄ አቅርበው ነበር። የአሜሪካ መንግሰት ተወካይ " በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ብሄሮች በመንግስት የስልጣን ቦታዎች ፍትህዊ በሆነ መንገድ አልተወከሉም፣ ዋና ዋና የመንግስት ስልጣኖች በአንድ ብሄር የተያዙ ናቸው" ሲሉ አስተያየት ከሰጡ በሁዋላ፣ በቅርቡ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ለማፈን የወጣውን ህግም ክፉኛ ተችተውታል። ተወካዩ በኦጋዴን ያለውን የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ሁኔታ፣ በህጻናት ላይ እየተፈጸሙ ስላሉ ወንጀሎችም አንስተው የወያኔን አገዛዝ በመተች ጥያቄ ማቅረባቸውን የዲፕሎማቲክ ምንጮች ተናግረዋል።

የኔዘርላንድስ መንግስት ተወካይ በበኩላቸው መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ለማፈንና ሽብርተኝነትን አስመልከቶ የወጡት ህጎች የሰብአዊ መብቶችን እንደሚጥሱ ጠቅሶ፣ በኢትዮጵያ ሰዎች በፖለቲካ እምነታቸው ምክንያት እንደሚታሰሩ፣ በህጻናት ላይ ወንጀሎች እንደሚፈጸሙ ገልጿል። መጪው ምርጫ ፍትህዊና ነጻ በሆነ መንገድ ይካሄድ ዘንድ መንግሰት ለፖለቲካ ፣ ለእርዳታ እና ለሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች በነጻ የመንቀሳቀስ መብት መስጠት አለበት ብለዋል። የካናዳ መንገስት በበኩሉ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ እሰርኞች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲፈቱ ና መጪው ምርጫ ስርአት ባለውና ሁሉንም በሚያረካ መልኩ እንዲካሄድ የጠየቀ ሲሆን፣ የዩናይትድ ኪንግደም ተወካይ ደግሞ የጸረ ሽብርተኝነት ህጉ ና መንገስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን የሚመለከቱት ህጎች አለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶችን ደንብ የሚጥሱ መሆናቸውን አጽንኦት ሰጥተው ተናግረዋል። (**ወደ ገጽ 4 ዞሯል**)

## ግንቦት 7 በኮሎምበስ ኦሀዮ የተሳካ ስበሰባ አደረገ። ሰብሰባውን በኦሀዮ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በራስ አነሻሽነት ያዘጋጁት መሆኑም ታውቋል

ዶ/ር ብርሀኑ ነጋና አርቲስት ታማኝ በየነ በእንግድነት የተሳተፉበት ስብሰባ በኮሎምበስ ኦሀዮ መካሄዱን ከስፍረው የተላከው መረጃ አምልክቷል። ስበሰባውን በአካባቢው የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በራስ ተነሻሽነት ማዘጋጀታቸው የተገለጸ ሲሆን ፣ ከአዘጋጆቹ ለመረዳት እንደተቻለው ስበሰባው በሁሉም ረገድ እጅግ ውጤታማ ነበር። የአገራቸው በወያኔ እጅ ወድቃ መሰቃየት እንቅልፍ የነሳቸው በኦሀዮ ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያን እርስ በርስ ተጠራርተው ባዘጋጁት ስብሰባ በርከታ ሰዎች መገኘታቸውንም ከአዘጋጆቹ ሪፖርት ለማወቅ ተችሎአል። ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ "ወያኔ የሚያጠፋውን ጥፋት እያነሳን ጊዜያችን ማጥፋት የለብንም። መነጋገር ያለብን ምን ማድረግ አለብን በሚለው ዙሪያ ነው" ብለው ንግግራቸውን ያቀረቡ ሲሆን፣ አርቲስት ታማኝ በየነ ደግሞ ለምን ወያኔን መቃወም እንደሚገባ በመረጃ የተጠናቀረ ንግግር አቅርበዋል። በስብሰባው በብዙ ሺዎች የሚቆጠር ገንዘብ መሰብሰቡንና የአቋም መግለጫም መውጣቱን ለማወቅ ተችሎአል።

## የጉጅ ህዝብ በአላሙዲን የወርቅ ማውጫ ኩባንያ ላይ የተቃውሞ ሰልፍ አደረገ፣ የፌደራልና የክልል ፖሊሶች አካባቢውን ወርረው ህዝቡን በመደብደብ ላይ መሆናቸውን ከስፍራው ተዘግቧል

የግንቦት 7 የኦሮሚያ ወኪል ከትናንት በስቲያ በላከው መረጃ እንዳመለከተው በኦሮሚያ ክልል በጉጂ ዞን የሚገኙ ነዋሪዎችና ተማሪዎች በተሳተፉበት ታላቅ የተቃውሞ ስብሰባ፣ ሚድሮክ ኢትዮጵያ የተባለውን የአላሙዲንን የወርቅ ኩባንያና ወያኔን በአንድነት ሲያወግዙ ተሰምተዋል። ሰልፈኞቹ ሚድሮክ የተባለው ኩባንያ የአካባቢያችንን ወርቅ እየዘረፈ ቢገኝም በአካባቢያችን አንድም የልማት ስራ አልሰራልንም ፣ ወያኔም ሚድሮክን በመደገፍ የአካባቢያችን ህዝብ እንዲጎዳ እያደረገ ነው ሲሉ የተቃውሞ ድምጽ ማሰማታቸውን ሪፖርተራችን የዘገበ ሲሆን፣ የፌደራልና የክልል የፖሊስ አባላት በአካባቢው ተገኝተው ሰልፉን ለመቆጣጠር ሙከራ አድርገዋል። ወታደሮቹ ሰልፉን ለመበተን የሀይል እርምጃ መውሰዳቸውን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን የሟቾችንና የቁስለኞችን ቁጥር ይህ መረጃ እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ ለማወቅ አልተቻለም ። ይሁን እንጅ በርካታ ነዋሪዎች እንደተደበደቡ ከሰልፉም በሁዋላ አስተባባሪዎቹ ከእየቤታቸው እየተለቀሙ እንደተወሰዱ ሪፖርተራችን ዘግቧል። (**ወደ ገጽ 4 ዞሯል**)

## ወያኔን አስወግደን የፕሬስ ነፃነት የተረጋገጠባት ኢትዮጵያን ለመገንባት በጋራ እንነሳ!!!

ኢትዮጵያ ዉስጥ ፕሬስ ነፃ ሆኖ ባያውቅም በተለምዶ "ነፃ ፕሬስ" ተብሎ የሚጠራውና በወያኔ ቀጥታ ቁጥጥር ውስጥ ያልገባው የኢትዮጵያ ፕሬስ ላይ እየደረሰ ያለው ጥቃት እየከፋ መጥቷል። በዚህ ሳምንት ብቻ፡-

1. *የአዲስ ነገር ጋዜጣ አዘጋጆች* እንግልትና ወከባ ተቋቁመው እስካሁን ቢዘልቁም ሊሸከሙት የማይችሉት በደል እየተደገሰላቸው መሆኑን ሲያረጋገጡ ጋዜጣቸውን በድንገት ዘግተው ለስደት ተዳርገዋል፤
2. በምርጫ 97 ማግስት ከቅንጅት መሪዎችጋር ታስረው "ይቅርታ ተደርጎላችኋል" ተብለው የተፈቱት ጋዜጠኞች ክስ እንደገና ተንቀሳቅሶ እድሜ ልካቸውን ከፍለው ሊጨርሱት የማይችሉችን የገንዘብ መጠን ካልከፈሉ ወደ እስር ቤት የሚመለሱበት መንገድ እየተመቻቸ ነው፤
3. ለውጭ አገር ጋዜጦች ዜና የሚያቀርቡ ዘጋቢዎች ላይ ወከባው እጅግ በመብዛቱ አንዳንዶች አገር ለቀው ወጥተዋል፤ ሌሎቹም በቋፍ ላይ ናቸው፤
4. *የአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ* አዘጋጆች እየደረሰባቸው ያለው መንገላታት ከእለት ወደ እለት በከፍተኛ መጠን እየጨመረ ነው፤

በመንግሥት ጋዜጠኞችም ዘንድ ምሬት በረክቷል። እዚያም አፈና አለ፤ ከዚያም የተሰደደ አለ።

አገራችን ውስጥ ጋዜጠኞችን ማዋከብ፣ ማንገላታት፣ መቅጣት፣ ማሰርና፣ በጨለማ እያደፈጡ ማጅራት መምታት ዛሬ የተጀመረ ነገር አይደለም። እንዲያውም ከወያኔም በላይ እድሜ አለው። በዚህ ረገድ የወያኔን አገዛዝ ከሱ ቀደም ከነበሩት አገዛዞች የሚለየው በአደባባይ እያበረታታ በጎን ግን አበሳ የሚያሳይ መሰሪ አገዛዝ ነው። ወያኔ ሚኒሊክ ቤተመንግሥት ከከተመበት ጊዜ ጀምሮ በፕሬስ ላይ የጫነው አፈና እያጠበቀ ያለ መሆኑ የታወቀ ስለሆነ የሰሞኑ ኩነቶች ለምን የተለየ ትኩረት ተሰጣቸው የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። በኛ እምነት የሰሞኑ ሁኔታ በሚከተሉት ምክንያቶች ልዩ ትኩረት ይሻል።

### 1. ወቅቱ

ወያኔ በአሁኑ ሰዓት ሁለት ተቃራኒ ነገሮችን በአንድ ጊዜ በማስኬድ ውዥምብር እየፈጠረ ነው። በአንድ በኩል የምርጫ ስነምግባር መፈረምን ተከትሎ መሠረታዊ የአስተሳሰብ ለውጥ የተደረገ ይመስል "ከዜሮ ድምር ወደ ትርፋማ ድምር ፓለቲካ" ሰለተደረገ እመርታ የሚያብራሩ ነባርና አዳዲስ ሰባኪያንን በመጠቀም በኅበረተሰባችን ውስጥ አጠቃላይ የአስተሳሰብ ብዥታ ለመፈጠር ጥረት እያደገ ነው። "መቻቻል"፣ "መከባበር"፣ "ሰጥቶ መቀበል" እና የመሳሰሉትን ቃላት በመደጋገም የውጭ ታዛቢ እውነትም አዲስ አስተሳሰብ እየሰፈነ ይሆንን ብሎ እንዲጠራጠር ለማድረግ የቻለ ይመስላል። ወያኔ የውጭ ታዛቢዎችን ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያውያንንም ለማሳመን ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ነዉ። እናም በየቀበሌው በራፍ የነበሩ "ድህነትን ተረት እናደርጋለን" መፈክሮች "የመቻቻል ፓለቲካን እናሰፍናለን" በሚሉ እየተተኩ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ በወቅቱ ማደናገሪያ ሳይታለሉ በሰከነ መንፈስ ሁኔታዎችን ይከታተሉ ይሆናል ተብለው የተጠረጠሩ ተቋማትና ግለሰቦች ተለይተው እየተመቱ ነው። ለሥርዓቱ ያላጎበደዱ ሁሉ የሚዘገንን አረመኔዓዊ ድርጊት ይፈጸምባቸዋል። በወያኔ መፈክርና ተግባር መካከል ትስስር የሚባል ነገር የለም። ቢኖርማ ኖሮ ስለመቻቻልና መከባበር እየተሰበከ በነጄኔራል ተፈራ ማሞ ላይ ሰቆቃና ክብረ ነክ ተግባራት ባልተፈፀሙ ነበር፤ ወ/ት ብርቱካን ሚደቀሳም ያለአግባብ ለደረሰባት እንግልት ይቅርታ በተጠየቀችና ካሳም በተከፈላት ነበር። ከሰበካው ጎን ለጎን እየተደረገ ያለው ግን ተቃራኒው ነው። ወያኔ ሙሉ በሙሉ በእጁ ውስጥ ካልገቡ በስተቀር የገዛ ራሳቸውን ሳንሱር በማድረግ ሲጨነቁና ሲጠበቡ የሚውሉ ጋዜጠኞችን እንኳን ሥራቸውን እንዲሰሩ አልፈቀደም። ፈቃድ በመከልከላቸው የራሳቸው ጋዜጣ ባይኖራቸውም እጉያው ውስጥ ያልገቡ ጋዜጠኞች መኖር ብቻውን ያስፈራዋል። የወያኔ ቀልብ የሚፈራትን የምርጫ ጊዜ በውዥንብር ማለፍ ይፈልጋል።

### 2. ህግ

ይህ ሳምንት ህግ አልባነትን ህጋዊ የሚያደርገው የፀረ–ሽብርተኝነት ህግ ህዝብ የማሸበር ተግባሩን በይፋ የጀመረበት ነው ማለት ይቻላል። በዚህ ህግ መከሰስ ማለት በጥፋተኝነት መፈረጅ ማለት ነው። በመደበኛውም ህግ ቢሆን ሃቀኛ ነኝና ተከራክሬ እረታለሁ የሚል ብዙ ሰው ባይኖርም በህግ ላይ ተስፋ ያልቆረጡ ጥቂት ሰዎች ግን ነበሩ። በፀረ ሽብርተኝነት ህግ ግን ከሳሽ ያቀረበው ማስረጃ ሁሉ ተቀባይነት አለው፤ ፖሊስ ያለው ሁሉ እውነት ነው። የዚህ ህግ በሥራ ላይ መዋል በጥቂቶች ዘንድ በህግ ላይ የነበረው ትንሽ ተሰፋ ሙሉ በሙሉ ተሟጦ እንዲጠፋ አድርጎታል። ከዚህም በተጨማሪ የህጉ በሥራ ላይ መዋል ወይ የወያኔ ባለሟል አለያም ከህጉ ማእቀፍ የወጣ ተቃዋሚ እንጂ ከመሃል የሚገኝ ወይም ከማናቸውም ያልወገነ ሰው ወይም ተቋም እንዳይኖር አድርጓል። እንዲያውም የህጉ ግንባር ቀደም ተጠቂ በህግ ማዕቀፍ ሆነን ወያኔን እንታገላለን የሚሉ ወገኖች መሆናቸው ግልጽ ሆኗል።

### 3. ስፋቱ

አሁን በፕሬስ ላይ እየተወሰደ ያለው እርምጃ የሌላ መጠነ ሰፊ እመቃ መንደርደሪያ ሊሆን ይችላል። የሚቀጥሉት ሰለባዎች የስነምግባር ሰነዱን ባልፈረሙት ፓርቲዎች ሊሆኑ እንደሚችል ብዙ ፍንጮች እየታዩ ነው። የምርጫ ስነምግባሩን ብቻ ሳይሆን ውጤቱንም ጭምር በምስጢር ካልተደራደሩ በስተቀር ወያኔ ትንሽ ቆይቶ አሁን ውል ወደፈረሙትም መዞሩ አይቀርም።

እንደ ግንቦት7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ እምነት በአዲስ ነገር ጋዜጣ፣ በአዘጋጆቹና በጋዜጠኞች ላይ እየደረሰ ያለው ቅጥ ያጣ እንግልት ነገ በመላ ሕዝባችን ላይ የሚደርሰውን አመላካች ነው። ስለሆነም አፈናውን አምረን እንታገላለን። በዚህ አጋጣሚ ለመግለጽ የሚያዳግት ወከባን ተቋቁመው እየሠሩ ላሉ ጋዜጠኞችና አዘጋጆች ያለንን አድናቆት እንገልፃለን፤ ፍትህና ነፃነትን ናፋቂ የሆነ ሁሉ ከጎናቸው እንዲቆም ጥሪ እናደርጋለን።

እዚህ ላይ አጽንዖት የምንሰጠው እውነታ ወያኔ እስካለ ድረስ ለፕሬስ ነፃነት ዋስትና የሚሰጥ አንዳችም ተቋም የለም ብለን ማመናችን ነው። ለፕሬስ ነፃነት ዋስትና የሚሰጥ መንግሥት እንዲኖረን ወያኔን አስወግደን በምትኩ ፍትህና ሁሉም ነፃነቶች የተረጋገጡባት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን መገንባት ግድ ይላል። ይችን ኢትዮጵያ ለመገንባት ደግሞ ሁላችንም በጋራ እንነሳ!!!

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

## የመለስ ዜናዊ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ የአሜሪካ ባለስልጣናትን ለማሳመን በርካታ ሚሊዮኖችን በእያመቱ እንደሚያፈስ ከአሜሪካ ፍትህ ሚኒቴትር የተገኘው መረጃ አረጋገጠ

የአሜሪካ የፍትህ ሚኒስትር የመረጃዎች ክፍል እንዳሰፈረው የወያኔው አገዛዝ የአሜሪካ ባለስልጣናትን ለመደለል አምናና በዚህ አመት በጠቅላላው 6 ሚሊዮን ዶላር አውጥቷል። የአውሮፓ መንግስታትንና የአውሮፓ ህብረት ባለስልጣናትን ለመደለል የወጣው ገንዘብም ከዚህ መጠን እንደማይተናነስ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ይናገራሉ።

የወያኔው አምባገነን አገዛዝ አለኝ ይል የነበረው ህዝባዊ ድጋፉ በየጊዜው እየተሸረሸረበት በመምጣቱ ፤ ስልጣኑን ለማቆየት በውጭ ሀይላትና በመከላከያ ሰራዊቱ ላይ እንደሚተማመን ተደጋግሞ የተገለጠ መሆኑ የሚታወስ ሲሆን፣ የአሜሪካ የፍትህ ሚኒስቴር መስሪያቤት ያወጣው መረጃም ይህንኑ እውነታ በይበልጥ የሚያንጸባርቅ ነው። ወያኔ ከፍተኛውን ገንዘብ የከፈለው ዲኤል ኤ ፓይፐር፣ ዴዊይ ኤንድ ለበፍ እና ማርክ ሴይለር ለተባሉ ካምፓኒዎች መሆኑን መረጃው አመልክቷል።

ከ15 ሚሊዮን ህዝብ በላይ በተራበባት አገር ወያኔ ለውጭ አገር የድለላ ድርጅቶች ይህን ያክል ገንዘብ ማፍሰሱ አገዛዙ ምን ያክል ጨካኝና በንቅዘት የተሞላ ራስ ወዳድ መሆኑን ያሳያል የሚሉት አስተያየት ሰጪዎች፣ በየጊዜው ያልተቋረጠ ድጋፍ የሚሰጡት የውጭ አገር መንግስታት ራሳቸው የወያኔን ድርጊት ቆም ብለው መገምገምና እርምጃ መውሰድ ይኖርባቸዋል ብለዋል።

በየአመቱ የአሜሪካ ባለስልጣናትን በጥቅም ለመያዝ ለድላለ ስራ የሚወጣው ገንዘብ በቀን አንድ ዳቦ ተመግበው መኖር ላቃታቸው ወገኖቻችን ቢሰጥ፣ → የበርካቶችን ህይወት ለመታደግ የሚቻል መሆኑን አስተያየት ሰጪዎች አክለው ተናግረዋል።

በተያያዘ ዜናም አገዛዙ በ2007 አም ብቻ አርባ አንድ ሚሊዮን ዶላር በማውጣት ከአሜሪካ የጦር መሳሪያዎችን መሸመቱ አብሮ የደረሰን መረጃ አመልክቷል። ወያኔ 25 ሚሊዮን 200 መቶ ሺ ዶላር ለጦር ጀቶችና መለዋወጫ እንዲሁም 15 ሚሊዮን ዶላር ለኬሚካል፣ ባዮሎጂካልና ቶክሶሎጂካል ኤጀንትስ ግዢ ወጭ አድርጓል። ይህ አሀዝ ከሰሜን ኮሪያ፣ እስራኤል፣ ኢራን፣ ሩስያ፣ ዩክሬንና ቤላሩስ የተገዙትን የጦር መሳሪያዎች ወጪ አይጨምርም ተብሎአል።

አገዛዙ በስልጣን ላይ ለመቆየት ሙሉ እምነቱን በመከላከያውና በውጭ አገር መንግስታት ላይ መጣሉን እነዚህ ማስረጃዎች የሚያመልከቱ ሲሆን፣ ወያኔ እየተበደረ ለሚገዛቸው የጦር መሳሪያዎች፣ የማታ የማታ እዳ ከፋዩ አሁን ያለውና መጪው ትውልድ በመሆኑ የወያኔን አገዛዝ ዕድሜ ለማሳጠር ሁሉም ተግቶ መታገል እንዳለበት አስተያየት ሰጪዎች ይናገራሉ። የ ኢትዮጵያን ህዝብ ነጻነት ለማፈን ለሚገዛው መሳሪያ እዳ ከፋዩ ራሱ የኢትዮጵያ ህዝብ መሆኑ እንቆቅልሽ ነው የሚሉት አስተያየት ሰጪዎች፣ ህዝቡ ይህን ተገንዝቦ "የሥልጣን እድሜህን ለማራዘም በራሴ ገንዘብ በተገዛ ጦር መሳሪያ እየገደልከኝ አትኖርም" ብሎ በወያኔ ላይ አምጾ መነሳት አለበት ሲሉ ምክራቸውን ለግሰዋል።

በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን

የፖስታሳጥን ቁጥር ፡- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

# የመንግስታቱ ድርጅት የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ የአፍሪቃ በርካታ መንግስታት መለያ የሆኑትን የዲሞክራሲ እጦትና የመልካም አስተዳደር ችግሮች ያማከለ ዉይይት ሊያደርግ ይገባዋል

ዓላማው አንድ ቢመስልም በሁለት ጎራዎች ለተከፈሉ አበይት ምክንያቶች በከፍተኛ ደረጃ በጉጉት ሲጠበቅ የነበረው የመንግስታቱ ድርጅት የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ ወደ ሁለት መቶ የሚሆኑ የዓለማችን ሃገራት ከ15000 በላይ የሆኑ ልኡካኖች በተገኙበት ሰኞ ዲሴምበር 7 ቀን 2009 በኮፐን ሃገን ተጀምሮአል። በዚሁ ስብሰባ ላይ በዓለማችን በተለይም በአፍሪቃ በአምባገነንታቸው ከሚታወቁት መሪዎች ዋናው የሆነው የወያኔው ቁንጮ መለስ ዜናዊ 52 የአፍሪቃ ሃገራትን ድምጽ ወክሎ የሚገኝ ሲሆን ከኢትዮጵያ ምድር ዶላር አንፍናፊ ሃይላትን ያካተተ 'የባለሙያዎች ባታሊዮን ጦር' አሰልፎና 'ከተት ሰራዊት ምታ ነጋሪት'ን አሳውጀ 'ተዋጊ ጦሩ' ዴንማርክ ላይ እንዲሰፍር ካደረገ ቀናቶች ተቆጥረዋል።

የሰው ልጅ ሰብአዊ መብቶች በማይታመን ሁኔታ እየተረገጡባት ያለችን ሃገር 'እየመራ' ያለ አምባገነን፤ በዘር ማጥፋት ወንጀል ሊጠየቅ እንደሚገባው በተለያዩ የዓለም አቀፍና የሃገር ዉስጥ ሰብአዊ መብት ድርጅቶች ጥያቄ የቀረበበት ዘር አጥፊ፤ ዘርን መሰረት ያደረገ መርዘኛና ከፋፋይ አገዛዝን በመከተል የወደፊቱን የሃገራችንን ተስፋ እጅግ በሚያስፈራ መልክ እያጨለመ ያለ ዘረኛ፤ በብዙ አስር ሺሆች ለሚቆጠሩ ንጹህ ኢትዮጵያዊያን ዜጎች ሞት ወይም በአሰቃቂ ሁኔታ በእስር መማቀቅ ተጠያቂ የሆነ አረመኔና እንኩዋንስ ለአካባቢ የአየር ንብረት ችግር ለሰብዓዊ ፍጡራን ቅንጣት ታክል ደንታ እንደሌለው የተረጋገጠለት መለስ አፍሪቃን በመወከል በኮፐን ሃገኑ ጉባኤ እንዲገኝ መደረጉ ከማሳፈሩም በላይ 'አፍሪቃ ለዚህ ጉባኤ የሚመጥን ሌላ ተወካይ አጣች ወይ?' የሚል ጥያቄን በርካታ ወገኖች እንዲያነሱ አድርጓል። በዚህም ምክንያት ወደዓለም አቀፉ ፍርድቤት ተከስሶ መቅረብ የሚገባው ዘር አጥፊ አፍሪቃን በመወከል የአየር ንብረት ተሟጋች ሆኖ የመቅረብ ብቃት እንደሌለውና የድርጊቱንም አሳፋሪነትን ለማጋለጥ እውነተኛ ኢትዮጵያዊያን ከፍተኛ የሆነ ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ ዝግጅታቸውን በማጠናቀቅ ላይ ይገኛሉ።

መለስ ዜናዊ በህልሙ ሳይቀር የሚያቃዠውን የገንዘብ ማግበስበስ አባዜ እዉን ለማድረግ የማይቆፍረው ጉድጓድ የለም። አሁንም ከኮፐን ሃገኑ ጉባኤ ዳጎስ ያለ ዶላርን ማፈስ ይችል ዘንድ በኢትዮጵያ 'መንግስታዊ ያልሆነ ድርጂት' በሆነው የአካባቢ ተቆርቋሪዎች መድረክ ሽፋን ከሁለት ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ 'ኢትዮጵያዊያን' ፊርማ እንዲሰባሰብና ለፕሬዘዳንት ባራክ ኦባማ እንዲላክ ያደረገ ሲሆን በሌላ በኩል በዚሁ ዓመት አዲስ አበባ ሂልተን አዳራሽ በተደረገው ክላይሜት አፒል ጉባኤ አሻንጉሊቱን ፕሬዘዳንት ግርማ ወልደ ጊዮርጊስን ጨምሮ የአካባቢ ጉዳይ ሊመለከታቸው ይችላሉ ተብለው የተገመቱ የዉጭና የሃገር ዉስጥ ድርጂቶችን፤ ታዋቂ ሞዴሊስቶችን፤ አርቲስቶችንና አትሌቶችን ሳይቀር በማሰባሰብ 'ድጋፋቸዉን' እንዲሰጡ አድርጓል። በዚሁ ስብሰባ ላይ አሻንጉሊቱ ፕሬዘዳንት ባደረገው ንግግር የዓለማችን የአየር ንብረት ለዉጥ ካደረሰብን ጥፋቶች ዋነኛው የኢኮኖሚ አቅማችንን ማዳከሙ በመሆኑ ዋናውና ወሳኙ ነገር 'ዶላሩ' ነው በማለት የአለቃዉን 'የዶላሩን ነገር አደራ' መልእክት አስተላልፏል። (ምናልባት) በይፋ ባይገለጽም ጳጳሱ ለነፍሳቸው ሳይሆን ለሆዳቸው ካደሩ ደቀ መዛሙርቶቻቸው ጋር በመሆን የ'ዶላሩን ወደኛ' ሱባኤ ላይ እንደተቀመጡም ይጠረጠራል።

እየተካሄደ ያለው የመንግስታቱ ድርጅት ጉባኤ የመጀመሪያ አይደለም የመጨረሻም አይሆንም። መሰል ጉባኤዎች እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር በ1995 ለመጀመሪያ ጊዜ በርሊን ላይ ቀጥሎ በ1996 ጀኔቫ ላይ በአየር መበከል ዙሪያ ላሉ ችግሮች ሃብታም ሃገራት የተናጠል ርምጃን በሚወስዱበት ሁኔታ ላያ የመከረ ሲሆን ኪዮቶ ላይ በ1997 በተካሄደው ስብሰባ ደግሞ የኪዮቶ ፕሮቶኮል እንዲዘጋጅ ሆኗል። በኪዮቶው ስብሰባ ወደ 37 የሚሆኑ ሃብታም ሃገራት የካርበን ልቀት መጠናቸዉን እስከ 2012 ባለው ጊዜ 40% በሚሆን መጠን እንዲቀንሱ ስምምነት ላይ ተደርሶ የነበረ ቢሆንም እስከ 2005 ድረስ አሜሪካን ጨምሮ በአንዳንድ ሃገራት የኪዮቶው ስምምነት በጎ ፈቃደኝነትን ሳያገኝ ቆይቷል። ከዚህ በሁዋላ ቦነስ አይረስ ላይ በ1998 እንዲሁም ቦን ላይ በ1999 በቴክኒካዊ ጉዳዮች (አፈጻጸሞች) ላይ ትኩረት ያደረጉ ስብሰባወች ከተካሄዱ በኋላ በ2000 ላይ ግዴታቸዉን ለመወጣት በጎ ፈቃደኝነትን ባላሳዩ ሃብታም ሃገራት ላይ ጫና የሚፈጥርና የሚያስገድድ ሁኔታን አመቻችቷል። በመቀጠልም ቦን፤ ማራከሽ፤ ዴልሂ፤ ሚላን፤ ቦነስ አይረስ፤ ሞንትሪያል፣ ናይሮቢና ባሊ ላይ እስከ 2007 ተከታታይ ጉባኤዎች የተካሄዱ ሲሆን በመጨረሻ በ2008 ፖዝናን ላይ የተደረገው ጉባኤ አሁን በመካሄድ ላይ ላለው የኮፐን ሃገኑ ስብሰባ መሰረታዊ ሁኔታዎችን የማመቻቸት ተግባር አከናውኗል።

የሁሉንም ሃገራት ህዝቦች ልብ በከፍተኛ ሁኔታ አንጠልጥለው ከሚገኙት በርካታ ጥያቄዎች ውስጥ የዓለማችን ሃብታም ሃገራት መሪዎች በርግጥም ሃላፊነቱ ተሰምቶአቸው ሊወስዱ የሚገባዉን ርምጃ ይወስዳሉን? እነኝህ ሃብታም ሃገራት የገቡበትን ታሪካዊ አጣብቂኝ ለመጠቀም ለቋመጡት የመለስ አይነት ብልጣብልጥ የአፍሪቃ መሪዎች እንደፍላጎታቸው መልስ ይሰጣቸው ይሆን? በዓመት እስከ 600 ቢሊዮን ዶላር ኪሳራን ሊያስከትል የሚችለው የጋስ ልቀት መጠን ቅነሳና ድሃ ሃገራትም እያቀረቡ ያለው ከፍተኛ የሆነ የገንዘብ ካሳ ውስብስብ የሆኑትን መሰናክሎች ማለፍ ይችል ይሆን? የሚሉትና ሌሎችም ይገኙበታል። በመሰረቱ የዓለማችን የዓየር ንብረት ለዉጥ በዓለማችን ላይ ሊያደርስ የሚችለውን ጥፋት እንዲህ በቀላሉ መተንበይና የጥፋቱንም ደረጃ በትክክል ማስቀመጥ ወይም መግለጽ በፍጹም የሚቻል አይደለም። ለዚህም ችግር ዋነኛ ከሆኑት ምክንያቶች በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት ለአደጋ መፈጠር መንሴ ናቸው የሚባሉት እንደ ድርቅና ጎርፍ መጥለቅለቅ ያሉ ክስተቶች በአንድ ወይም ከአንድ በላይ ሊሆኑ በሚችሉ ሌሎች ምክንያቶች ሊከሰቱ መቻላቸው አንዱ ሲሆን የዓለማችን የወደፊት የሃይል ምንጭ ምን ይሆናል? አጠቃቀሙስ ምን ሊመስል ይችላል የሚሉ ጥያቄዎችን አስቀድሞ መተንበይ አለመቻሉ ደግሞ ሌላው ችግር ነው፡፡ ያም ሆነ ይህ ያሁኑ የኮፐንሃገን ጉባኤ ለአራት ዋና ዋና አጠቃላይ ጥያቄዎች አጠቃላይ መልስ ያስገኛል ተብሎ ይጠበቃል። እነኝህም:-

- በሃብት የበለጸጉ ሃገራት የጋስ ልቀት መጠናቸውን በምን ያህል ፐርሰንት ለመቀነስ ፈቃደኛ ይሆናሉ?
- የቻይና አይነት በኢንደስትሪ በማደግ ላይ ያሉ ሃገራት እድገታቸዉንና የጋዝ ልቀት መጠናቸውን በምን ያህል ይገታሉ?
- በአፍሪቃና ሌሎችም ክፍለ ዓለማት ለሚገኙ ድሃ ሃገራት የሚያስፈልገው የገንዘብ ዕገዛ መጠን ምን ያህል ነው?
- ለድሃ ሃገራት የሚሰጠው ገንዘብ በምን ዓይነት መንገድና ሁኔታ ለታሰበለት ጥቅም ይውላል? የሚሉት ናቸው።

የእነኝህ ጥያቄዎች በጣም ውስብስብ መሆን ጉባኤው ሊደርስበት የሚችለዉ ስምምነት ይህ ይሆናል ብሎ መገመትን ከባድ አድርጎታል። አንዳንድ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት የተወሰኑ ሃገራት ተጨማሪ የገንዘብ ድጎማ ለድሃ ሃገራት የመስጠት ፈቃደኝነታቸው እጂግ አጠራጣሪ መሆኑን የገለጹ ሲሆን በሌላ በኩል ድሃዎቹ ሃገራት የጠየቁትን ተጨማሪ ገንዘብ ሃብታም ሃገራት ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆኑ በጉባኤው ስምምነት ላይ ላይደርስ ይችላል የሚል ስጋትም አለ።

ማንኛውም ሰብአዊ ፍጡር ንጽህናው በተጠበቀና ባልተበከለ፤ ጤናማና ምቹ የአየር ንብረት (ኢንቫይሮንመንት) የመኖር መብት እንዳለው የተደነገገ ቢሆንም መለስ እንኩዋንስ እነኘህን ኢንቫይሮመንታል መብቶች ሊያከብርም ሆነ ሊያስከብር ይቅርና በ21ኛው ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያዊያን የአሰቃቂና የግፍ ኑሮን እንዲጋቱ እያደረገ ያለ ፍጡር ነው። በዚህም ምክንያት ወያኔ ስልጣን ከጨበጠ ወዲህ በኢትዮጵያ የደን ጭፍጨፋና የአፈር መከላት ባስከፊ ሁኔታ ስለመባባሳቸው እንጂ የመሻሻል ሁኔታ ስለማሳየታቸው የሚያረጋግጥ ተአማኒነት ያለው መረጃ ካለመኖሩም በላይ የኢትዮጵያ ተፈጥሮ ሃብት ባስከፊ ሁኔታ እንዲያሽቆለቁል ከፍተኛዉን አስተዋጾ እያደረጉ ካሉት ክስተቶች የሚከተሉትን እንጥቀስ።

- የአካባቢ ጥበቃ የይስሙላ ፖሊሲ ደካማ መሆን የሃገሪቱ የተፈጥሮ ሃብት ከመቸዉም ጊዜ በላይ በከፋ ደረጃ ለመራቆቱ ምክንያት ሲሆን የሃገሪቱ የመሬት አስተዳደር ፖሊሲ ደግሞ ራሱ በተፈጥሮ ሃብት አያያዝና ጥበቃ ላይ ከፍተኛ ጥፋትን እያስከተለ ያለ ነው፡፡ በዚህ ደካማ የሆነ የመሬት ፖሊሲ ላይ የኢንደስትሪያላይዝድ ግብርና ጅምር እንቅስቃሴ መጨመር ደግሞ ሃገሪቱን ወደከፋ ደረጃ ሊያመራት እንደሚችልም መገመት አይከብድም።
- ወያኔ እያወቁም ሆነ ሳያውቁ ለሚታለሉለት ምእራባዊያን የሚያቀርባቸው በወረቀት ላይ የሰፈሩ ፖሊሲዎች በርግጥም ወያኔን ለማያውቀው እዉነት ሊመስሉ ይችላሉ። ይሁን እንጂ በዚሁ ዓመት አዲስ አበባ ላይ በተደረገ ስብሰባ ከባለስልጥኑ በቀረበ ሪፖርት የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲ በወረቀት ላይ ከመስፈር በዘለለ ሁኔታ ተግባራዊ ርምጃን ለመውሰድ እጅግ ውስብስብ የሆኑ ደንቃራዎች እንዳሉትና ፖሊሲዉም አጣብቂኝ ዉስጥ እንደሆነ ደይሊ ሞኒተር የተባለው የእንግሊዝኛ ጋዜጣ ማርች 13፣ 2009 ባወጣው ጽሁፉ አጋልጧል።
- ወያኔ እስካሁን ባወጣቸው ፖሊሲዎች ዙሪያ የኢትዮጵያን ህዝብ ይሁንታ ያላገኘ ከመሆኑም በላይ እንደጨለስ አባይ፤ ግልገል ጊቤና ሌሎች ግድብ ስራዎች ሲከናወኑ የይስሙላ እንጂ ደረጃውን የጠበቀ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ካለመከናወኑም በተጨማሪ የግንባታ ስራ ኮንትራቶችም ሻጥር ተሰርቶባቸውና ከኢትዮጵያም ህዝብ ተደብቀው በመፈጸማቸው ወደፊት ሊያስከትሉት የሚችሉዋቸው ጥፋቶች በቀላሉ የሚታዩ አይደሉም።
- ከአዲስ አበባ በ75 ኪ.ሜ ርቀት ላይ የሚገኘው የቆቃ ዉሃ መበከልና በአካባቢው ህብረተሰብ ላይ ያደረሰው የህይወት ጥፋት ለወያኔ ምንም ደንታ ያልሰጠው ከመሆኑ በላይ በቅርቡ ዘመቻ እየተካሄደበት ያለው የለም መሬቶች ሽያጭ (ኮንትራክት ፋርሚንግ) የሚተገብረው የኬሚካል ግብርና እንኩዋንስ የሃገሪቷን ችግር ሊያቃልል ቀርቶ የሃገሪቱዋን አንጡራ ሃበት በከፍተኛ ሁኔታ ከማራቆት ባለፈ መልኩ በአካባቢ ላይ ሊታጠፍ የማይችል የተፈጥሮ ሃብት መበከልን ማስከተሉ አይቀሬ ነው።

በአጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱት ነጥቦች የወያኔው ቁንጮ እንኩዋንስ አፍሪቃን በመወከል የአየር ንብረት ተሟጋች ሆኖ መቅረብ ይቅረብና 'እየመራት' ባለችው ኢትዮጵያ ያለውን ከአየር ንብረት ችግር ጋር የተያያዘ ብልሹ ሁኔታ ለማስተካከል ያልሞከረ ወይንም እንዲስተካከል ያልፈለገና ብቃት የሌለው ግለሰብ ለመሆኑ ማረጋገጫዎች ናቸው።

በኢትዮጵያ የለመደውን የአምባገነንነት ባህሪ እንደያዘ በጉባኤው የሚገኘው መለስ ወደስምምነት ከሚያደርሱ ነጥቦች ይልቅ እኔ ያልሁት ካልሆነ በሚል ግትር አቋም ችግር ሊፈጥር እንደሚችልም ይጠበቃል። ለዚህም መረጃ ይሆኑን ዘንድ ቀደም ብሎ ሃብታም ሃገራት ጥያቄአችንን ተቀብለው የማስተናገድ ቁርጠኝነትን የማያሳዩ ከሆነ ስብሰባ ረግጠን ልንወጣ እንችላለን ብሎ መዛቱን፤ ኖቨምበር 2009 ባርሴሎና ላይ በተደረገው ስብሰባ ሃብታም ሃገራት ወደፊት ለመቀነስ ያሰቡት የካርበን ልቀት መጠን በጣም ዝቅተኛ ነው በሚል የአፍሪካ ሃገራት በስብሰባው አለመገኘታቸው፤ በዚህም ምክንያ ከኮፐንሃገኑ ስብሰባ በፊት ሊሰራባቸው ታቅደው የነበሩ ቴክኒካዊ ተግባራት እንዲሰረዙ መደረጋቸውን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል። ይህም በመሆኑ በወቅቱ ስብሰባ የተገኙ የተለያዩ ሃገራት ወኪሎች የአፍሪቃ ጥያቄ ትኩረት ተሰጥቶት መፍትሄ ካልተፈለገለት በስተቀር ኮፐን ሃገን ላይ የሚደረገው ስብሰባ እንቅፋት ሊገጥመው ይችላል የሚል ስጋት ያደረባቸው መሆኑን የተገነዘቡት የመለስ አይነት ብልጣብልጥ መሪዎች ትእቢት አዘል ሽፍንፍን የካሳ ጥያቄ ክርክርን እያቀረቡ ይገኛሉ።

ከአፍሪቃዊያን በተለይም ከኢትዮጵያዊያን የወደፊት ህይወት ጋር ካለው ቀጥተኛ የሆነ ትስስር አንጻር ኢንቫይሮንመንት በአፍሪቃም የ21ኛው ክፍለ ዘመን ቀዳሚ አጀንዳ መሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም። ይሁን እንጂ የመልካም አስተዳደርና የዲሞክራሲ እጦት ባለበት እንዲሁም ብልሹ የሆኑ ፖሊሲዎች በግልጽ በሚታዩበት ሁኔታ ወደአፍሪቃ ፈሰስ ይደረጋል ተብሎ የሚጠበቀው ከፍተኛ ገንዘብ መፍትሄ ካልተፈለገለትና ብልሃት ካልተበጀለት በስተቀር ገንዘቡ የታለመለትን ግብ ከመምታት ይልቅ አምባገነኖቹ አገዛዛቸዉን እንደሚያጠናክሩበትና ዉጤቱም ወዳልተፈለገ የከፋ አቅጣጫ እንደሚያመራ የሚያጠራጥር አይደለም። የአፍሪቃ በርካታ መንግስታት መለያ የሆነዉን የዲሞክራሲ እጦትና አስተዳደራዊ ችግር ሽፋፍኖ በዓለም አቀፉ የሙቀት መጨመር ችግር ላይ ብቻ ማተኮር ዘለቄታዊ ዉጤትን የማያመጣ ከመሆኑም በላይ ምን ያህሉ የአፍሪቃዊያን ችግሮች በአምባገነኖች ምክንያት የተፈጠሩ ናቸው? ምን ያህሉስ በዓለማችን ሙቀት መጨመር የተከሰቱ ናቸው የሚሉት ነጥቦች በጥልቀት ሊፈተሹ ይገባቸዋል። በመሆኑም ሃብታም ሃገራት ጥንቃቄና ትኩረት የተሞላበት የቁጥጥር ዘዴ በመዘርጋት የሚደረገው የገንዘብ ካሳ የዲሞክራሲ ስራአትና የመልካም አስተዳደር መስፈንን ያማከለ እንዲሁም ሲቪክ ማህበራት በገንዘብ አሰባሰብና አጠቃቀም ረገድ ድምጽ እንዲኖራቸው ዕድል የሚሰጥ ሊሆን ይገባዋል።

## የወያኔው የደቡብ ህዝቦች ተወካይ ሽፈራው ሽጉጤ በአሜሪካን አገር ሊያካሂድ የነበረው ስብሰባ በግንቦት 7 አባላትና ደጋፊች ተቃውሞ ተጨናገፈ

በመሬት ድለላ ስም በውጭ አገር የሚገኙ ኢትዮጵያውያንን ለማማለል ጥረት የሚያደርገው ወያኔ፣ ሰሞኑን በዴንቨር አሜሪካ ሊያደርገው የነበረው ስብሰባ በግንቦት 7 ወጣት አባላት እንዲጨናገፍ ሆኑዋል። ስብሰባው የተጨናገፈው ወጣቶቹ ባሰሙት ተቃውሞ ሲሆን፣ በስፍራው የተገኙ የወያኔ አባላትም ተሸማቀው ወደ መጡበት ተመልሰዋል።

## የኢትዮጵያው አምባገነን መለስ ዜናዊ በቢሊዮን የሚቆጠር ዶላር ለማደን ወደ ኮፐን ሀገን መጓዙ አእምሮን በእጅጉ የሚረብሽ ነው ሲል አንድ ታዋቂ የውጭ አገር ጋዜጠኛ ተናገረ

በአሜሪካ ሚኒሶታ ነዋሪ የሆነው ጋዜጠኛ ዶክ ማክ ጊል (Douc McGill) ሰሞኑን ባወጣው ጽሁፍ ዘረኛውንና አምባገነኑን መለስ ዜናዊ በእጅጉ ተችቶታል። "ዛሬ" ይላል ማክ ጊል" ዛሬ የራሴን የጽሁፍ መመሪያዎች ልጥስ ወሰኛለሁ። ለአለፉት ስድሰት አመታት ስለኢትዮጵያ ስደተኞች ስጽፍ፣ በመለስ ዜናዊ ላይ ያነጣጠረ ጽሁፍ ጽፌ አላውቅም። እስካሁን ሳደርግ የነበረው የኢትዮጵአውያን ስደተኞችን ሀሳቦች ማንጸባረቅ ነበር። ዛሬ ግን የተለየ መንገድ መርጫለሁ። ይህንንም ለማድረግ የተገደድኩት መለስ በቅርቡ እያሳየ የመጣው አለማቀፍ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ለኢትዮጵያ፣ ለአፍሪካና ከዚያም አልፎ ለአለም አስጊ ነው ብየ በማሰቤ ነው" ብሎአል ለምን መለስ ዜናዊን በግል ለመተቸት እንደወሰነ ሲያስረዳ። ጋዜጠኛ ማክ ጊል ሲቀጥልም "አሁን መናገር የምፈልገው መለስ ዜናዊ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአየር ለውጥ ጉባኤ ላይ ተገኝቶ መድረኩን በጠራራ ጸሀይ ለመስረቅ ስለሚያደርገው ሩጫ ነው። የ52 አፍሪካ አገሮች ተወካይ በመሆኑ የኮፐን ሀገኑን ስብሰባ ለማጨናገፍ የሚችል ስልጣን ተሰጦታል። ከዚህ በፊትም በመቶዎች ቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ የጠየቁት ካልተሟላ ከስብሰባው ረግጦ እንደሚወጣ አሳውቆ ነበር። በእውነት የአለማችን ጨቋኝ አምባገነን ይህን ያክል ጉልበት ሲሰጠው መመልከት ያሳብዳል።"

የመለስን የአካባቢና የሰብአዊ መብቶች አያያዝን ሲተችም "መለስ አገሩን በከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲው ሰዎችን በማሰር በማሰቃየትና በመግደል እየገዛ ነው። ይህ ደግሞ አለማቀፍ ህብረት ለመፍጠር በሚደረገው ጉባኤ ላይ ጥላ ያጠላል። መለስ ለ18 አመታት ስልጣን ላይ ለመቆየት የቻለው ዘር በማጥፋት፣ አንድን ዘር ለይቶ በማጽዳት፣ ሰዎችን ወደ አሰቃቂ እስር ቤቶች በመላክ፣ የሀሰት ፍርድ ቤቶችን በመጠቀም፣ ሁዋላቀር የንብረት ህጎችን በመተግበርና ሲቪሎችን ና የፖለቲካ ሰዎችን እንደፈለገ በመግደልና በማሰቃየት ነው። ለመሆኑ ዴንማርክ ይህ አምባገነን ወደ አገሩዋ እንዲገባ እንዴት ትፈቅዳለች?" ብሎአል።

ጋዜጠኛ ማክ ጊል አያይዞም መለስ ዜናዊ በሚከተለው የተሳሰተ የአካባቢ፣ የህግና የፖለቲካ ፖሊሲ በርካታ ሚሊዮኖች በረሀብ እንዲጠቁ አድርጓል። ገበሬዎች የመሬት ባለቤቶች እንዳይሆኑ ከልክሎአል። የውጭ አገር ተመራማሪዎችና የእርዳታ ድርጅቶች እንዳይገቡ አግዷል። እኔ የምጠይቀው አለም እንዴት በዚህ ተንኮለኛና ጨካኝ አምባገነን ላይ አይኑን ለማሳረፍ አልሞከረም ፣ እንዴት የአለም ህዝብ ኢትዮጵያውያንን ለመታደግ አልተነሳም? የሚለውን ነው።" ሲል የመለስ ዜናዊን ወንጀልና የአለምን ምላሽ በማነጻጸር ጽፏል።

ጋዜጠኛ ማክ ጊል በመጨረሻም "መለስ ወደ ስልጣን እንደመጣ መጀመሪያ ያደረገው የተወሰኑ ዘሮችን ለይቶ ማጥፋት ነው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በሚወስዳቸው እርምጃዎች ሰውየውን በአለም ላይ ታዋቂ ከሆኑት አምባገነኖች ከእነ ኪም ጆንግ ኤል፣ ስሎቦዳን ሚሊሶቪች፣ ሙአመር ጋዳፊ፣ ሮበርት ሙጋቤ፣ ኦማር አል በሽር፣ ታን ስዌ እና አሊ ካሚኒ ተርታ አሰልፎታል። ታዲያ እነዚህ አምባገነኖች እንዲገኙ የማንፈቅድ ከሆነ እንዴት ሌላው አምባገነን በኮፐን ሀገን ስብሰባ እንዲገኝ እንፈቅዳለን? በርግጥ መለስ የሚፈልገው ለአፍሪካ ተከራክሮ ገንዘብ ማስገኘት አይደለም። እርሱ የሚፈልገው እንደገና ሙሉ በሙሉ ስልጣንኑን ተቆጣጥሮ ለመግዛት እንዲችል አለማቀፍ ድጋፍ ማግኘት ነው።" ሲል የመለስ ዜናዊን እውነተኛ ማንነት ለአለም ህዝብ ይፋ አድርጓል።

## አሜሪካ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ከፍተኛ የስልጣን ቦታዎች በአንድ ብሄር ሰዎች መያዛቸውን . . . ከገጽ 1 የዞረ

የፈረንሳይ ተወካይ በበኩላቸው በ1997 ምርጫ የተገደሉ ዜጎች ምርመራ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ፣ አምና በኦጋዴን የደረሰው ጭፍጫፋ እስካሁን ለምን ሊጣራ እንዳልቻለ እንዲብራራላቸው ጠይቀዋል። ጀርመን በበኩሏ በኢትዮጵያ ውስጥ ነጻ ሚዲያ የሚባል ነገር እንደሌለ ገልጻ፣ አገዛዙ ለሚዲያ ዋስትና እንዲሰጥ ጠይቃለች። የቤልጂየም ተወካይ በበኩሉ በኢትዮጵአ ያለው የሰብአዊ መብት አያያዝ ጥሩ አለመሆኑን ገልጾ፣ በተለይ ዜጎች በፖለቲካ እምነታቸው ምክንያት የእርዳታ እህል እንደሚከለከሉ፣ በኦጋዴን ሆን ተብሎ በተሰራ ደባ ህዘቡ እንዲራብ እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል። ለመሆኑ በምግብ ራሳችሁን ለመቻል ምን እያደረጋችሁ ነው? የመሬት ፖሊሲያችሁንስ እንዴት ታዩታላችሁ የሚል ጥያቄ ማቅረባቸውን የዲፕሎማቲክ ምንጮቻችን አክለው ተናግረዋል።

ለአምባሳደሩ የቀረቡት ጥያቄዎች በርካታ እንደነበሩ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን፣ አምባሳደር ፍስሀ ይመርም የተለመደውን የክህደት መልስ መስጠቱ ታውቋል። በኢትዮጵያ ውሰጥ ያለው የፖለቲካ ሁኔታ መሻሻሉን፣ መጪውን ምርጫ ነጻ ለማድረግም ከ65 ፓርቲዎች ጋር በቀርቡ የተፈረመው የስነምግባር ስምምነት የመንግስትን ወደ ትክክለኛ አቅጣጫ መጓዝ መጀመርን ያሳያል በማለት የምጸት ንግግር አድርጎአል።

## ዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ የምእራባዊያን የመገናኛ ብዙሀንና የእርዳታ ድርጅቶችን ወቀሰ

በሰብአዊ መብቶች ጥሰት አለምን በመምራት ላይ ያለው መለስ ዜናዊ የምእራብ አገሮች ጋዜጦችና የእርዳታ ድርጅቶች በአገሪቱ የያለውን ረሀብ ከመጠን በላይ እያጋነኑ ማቅረባቸው በእጅጉ እያበሳጨው መሆኑን ለታዋቂው ሙዚቀኛና የሰብአዊ ዕርዳታ ተማጋች ለሆነው ለሰር ቦብ ጊልዶፍ መናገሩን ኢንዲፐንደት የተባለው ድህረ ገጽ ዘግቧል።

በድህረ ገጹ ላይ በወጣው ዜና መሠረት መለስ ዜናዊ ለሰር ቦብ ጊልዶፍም ጭምር ማስጠንቀቂያ አዘል መልዕክት ሲሰጥ "ባንድ ኤድ በጊዜው አስፈልጎ ነበር። ልዩነት እንዳመጣችሁ ምንም ጥያቄ የለም፣ ነገር ግን ትብብር ወደ ምጽዋት ሲለወጥ ለአባቱም ለልጁም ጥሩ አይደለም። "ማለቱንና የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በኢትዮጵያ በዘንድሮው አመት 13 ሚሊዮን ህዝብ ተርቦአል ሲል ያወጣው መግለጫ በእጅጉ እንዳበሳጨው ዘግቦአል። "በርካታ ህዝብ ተርቦአል እያሉ መናገር ኢትዮጵያ አደገኛ ችግር ውስጥ ነች የሚል ምስል ይፈጥራል፣ ምናልባት የአለም አቀፍ ድርጅቶች በቂ እርዳታ ለማግኘት ቁጥርን እያጋነኑ ማቅረብን እንደዘዴ እየተጠቀሙበት ይሆናል። ነገር ግን ሁሌ ከፍተኛ ቁጥር እያቀረቡ ህዝብ ማሸበር ተገቢ አይደለም። እንዲህ ዓይነቱ ዘገባ በአገሪቱ ውስጥ ቋሚ የሆነ ቀውስ እንዳለ አድረጎ የሚያሳይ ነው" በማለት የተናገረው መለስ ዜናዊ በረሀቡ ምክንያት ምን ያክል ምስሉ እየተሸረሸረ እንደመጣ በተዘዋዋሪ መንገድ ማመኑን ያሳያል ተብሎአል።

አምባገነኑ መለስ "የኢትዮጵያ ረሀብ የተከሰተበትን 25ኛ አመት በማስታወስ የሚደረገው ጥረትና የሚዲያ ዘገባ በአገሪቱ ውስጥ ምንም ነገር እንዳልተሰራ ሁሉም ነገር እንደተንኮታኮተ የሚያሳይ በመሆኑ ሊወገዝ ይገባዋል " ማለቱም ተዘግቦአል። መለስ ዜናዊ ቦብ ጊልዶፍን ተቀብሎ ሲያናግር የተበላሸ ምስሉን እንዲቀይርለት ፈልጎ የነበረ ቢሆንም ፣ የአርቲስቱ ትኩረት ረሀቡ ላይ መሆኑ መለስን በእጅጉ እንዳበሳጨው ለማወቅ ተችሎአል። ቦብ ጊልዶፍ በመለስ ዜናዊ የሰብአዊ መብት አያያዝ ላይ ትልቅ ቅሬታ እንዳለውም ሳይሸሽግ ይናገራል።

ወያኔ በረሃ በነበረበት ወቅት ይቆጣጠር ለነበረው በድርቅ ለተጎዳው የትግራይ ክልል እንዲከፋፈል በሰር ቦብ ግልዶፍ ድርጅት አማካኝነት ከ100 ሚሊዮን ዶላር በላይ የገንዘብ እርዳታ እንደተሰጠውና በረሃቡ ምክንያት ህዝብ እንደቅጠል ሲረግፍ መለስ ዜናዊና ግብረአበሮቹ ለነፍስ አድን የተሰጠውን የእርዳታ ገንዘብ ለጠባብ አላማቸው ማስፈጸሚያ ይገነቡት ለነበረው ጦር እንዳዋሉት የህወአት ከፍተኛ አመራር አባላት የነበሩት አቶ ገብረመድህን አረአና አረጋዊ በረሄ በቅርቡ በጻፉት ጽሁፍ ማጋለጣቸው አይዘነጋም።

## የአዲስ ነገር ጋዜጣ ቢሮ በወያኔ ደህንነቶች . . . ከገጽ 1 የዞረ

የነበሩት አይነት ጋዜጦች እንዳይፈጠሩ ካደረገ በሁዋላ ሲሆን፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን በወያኔ ላይ ጠንካራ ትችት ማቅረብ ጀምሮ የነበረውን አዲስ ነገር ጋዜጣን እንዲዘጋ ማስደረጉ ፣ወያኔ አሁንም በራስ መተማመን እንደሌለው ያሳያል ሲሉ አስተያየት ሰጪዎች ይናገራሉ። ነጻ ሚዲያ በሌለበት ምንም አይነት ነጻ ምርጫ ማካሄድ አይቻልም የሚሉት አስተያየት ሰጪዎች፣ በዘንድሮው አመት የሚካሄደው ምርጫም ከአሁኑ ውድቅ ሆኗል ሲሉ አስረድተዋል። በኢትዮጵያ ውስጥ ነጻና ፍትሀዊ ምርጫ ለማድረግ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ፈጽሞ የሉም የሚሉት አስተያየት ሰጪዎች፣ ፍርድቤቶች፣ ፖሊስ፣ መከላከያና የደህንነት ተቋማት እንዲሁም ሚዲያውና ምርጫ ቦርድ በወያኔ ቁጥጥር ስር መሆናቸውን ለአብነት ጠቅሰዋል።

ህብረተሰቡ በይስሙላ ምርጫ መሳተፍ እንደሌለበት ያሳሰቡት አስተያየት ሰጪዎቹ፣ በይሉንታ ወይም በግዴታ ምርጫ ውስጥ ገብቶ የሚመርጥ ከሆነ ግን፣ የወያኔን እድሜ በማራዘም በዚያው ልክም የራሱንም ስቃይ ያራዝማል ሲሉ ተናግረዋል።

## የጉጅ ህዝብ በአላሙዲን የወርቅ ማውጫ ኩባንያ ላይ የተቃውሞ ሰልፍ አደረገ . . . ከገጽ 1 የዞረ

ጉጂ በነጌሌ ቦረናና ክብረ መንግሰት አካባቢ የሚገኙ ህዝቦች ሲሆኑ በኢትዮጵያ ውስጥ ድህነት እጅግ ካጠቃቸው ህዝቦች መካከል የሚመደቡ ናቸው። ሚዲሮክ ኢትዮጵያ በአካባቢው ትልቅ የወርቅ ማእድን ፕሮጀክት ያለው ሲሆን፣ በእያመቱም ከዚሁ የወርቅ መአድን በመቶ ሚሊያኖች የሚቆጠር ገንዘብ ያፍሳል። ሪፖርተራችን እንደገለጸው ህዝቡ ትምህርት ቤቶች ፣ ጤና ኬላዎችና ሌሎችም መሰራተዊ የሆኑ የልማት ተቋማት ይገነቡልናል ብሎ ቢጠብቅም፣ እስካሁን ድረስ የተደረገለት ምንም ነገር የለም። ሚድሮክ በአካባቢው የዘረጋው ፕሮጀክት አካባቢውን እየበከለው በመምጣቱ የመሬቱ ምርታማነት መቀነሱንም ነዋሪዎች ማናገራቸውን ዘጋቢያችን ገልጿል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**በ 7530 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ** እና **በ 9610 KHZ በ 31 ሜትር ባንድ** ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን g7radio@ginbot7.org ወይም በስልክ ቁጥር 0044- 203-286- 9661